**ማርች 2018 QuickNotes ቁ. 1**

**የሚቀጥለው የMCPS የአመቱ መምህር ማን ይሆናል/ትሆናለች?**

በማርያን ግሪንብላት የትምህርት ፈንድ (Marian Greenblatt Education Fund) ለሚደረገው የ2018 - 2019 የዓመቱ መምህር ተሸላሚነት ሦስት መምህራን ለፍጻሜ ተወዳዳሪነት ተሰይመዋል። እነርሱም፦ ክርስቲን ኬን/Kristen Kane በፎረስት ኖልስ ኤለመንተሪ ት/ቤት/Forest Knolls Elementary School የሙዓለ ሕጻናት መምህርት፣ኤድዊና ኤ. ኮሎ/Edwina A. Kollo በሼዲ ግሮቭ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Shady Grove Middle School የሂሳብ ይዘት/ኮንተንት ስፔሻሊስት እና ጃነት ጋልግኸር/Janet Gallagher በቤተዝዳ ቼቪ-ቼዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት/Bethesda-Chevy Chase High School የሪሶርስ መምህርት።

Kristen Kane በፎረስት ኖልስ/Forest Knolls ከ2011 ጀምሮ የሙዓለ ህጻናት እና የአንደኛ ክፍል መምህርት ናት። በተጨማሪም የሙዓለ ህፃናት የቡድን መሪ እና የሰራተኞች/staff እና የPTA(የወላጅ መምህር ህብረት) አገናኝ/liaison ናት። ተባባሪ፣ ታጋሽ፣ እና ሃሳቧን የምታንፀባርቅ መምህርት ናት። ከተማሪዎቿ ጋር ጠንካራና መልካም ግንኙነት በመገንባት ጥሩ የሚያንጓ የመማሪያ ክፍል በመፍጠር ተማሪዎችን የሚያሳትፉቸው ትምህርት ታቀርባለች። እርሷ የምታስተምርበት ክፍል ደስታ የሰፈነበት፣ ሞቅ ያለ እና አሳታፊ ነው። በተጨማሪም የሙዓለ ህፃናት የቡድን መሪ እና የሰራተኞች/staff እና PTA(የወላጅ መምህር ህብረት) አገናኝ/liaison ናት። ልዩ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የመማር ስንክልና፣ የንግግር እና የቋንቋ ዘገምተኝነት እና የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሆነው በእንግሊዝኛ ከሚማሩ ጋር የመሥራት ጥሩ ችሎታ አላት።

— Kane በተመለከተ ቤታኒ ዲ.ሚለር (Bethany D. Miller) የተባሉ አንድ ወላጅ በጻፉት አስተያየት፤ ለጥሩም ይሁን ለመጥፎ ሰዎች ሁሉ የመጀመሪያ ኤለመንተሪ ት/ቤት መምህራቸውን ያሳታውሳሉ፣ "Everyone remembers their first elementary school teacher, for better or for worse," parent Bethany D. Miller wrote on Kane's behalf. "Mrs. Kane ልጆቼን በፍቅር በማበረታታትና በማነቃቃት እንዲማሩና እንዲያድጉ በመርዳቷ በበቂ ለማመስገን ያቅተኛል። ይህንን ለምታስተምራቸው ልጆች በሙሉ እንደምታደርግ አውቃለሁ።"

Edwina A. Kollo ሥራዋን የጀመረችው በ securities-backed lending and education sales መስክ ነው። እንደ የረጅም- ጊዜ ተተኪ በመሆን ወደ ማስተማሩ ዓለም ተዛወረች እናም ወደደችው። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪን በደንብ ትገነዘባለች፣ ስለዚህ ከተማሪዎቿ ጋር መልካም ግንኙነት ለመገንባት በምታደርገው ጥረት በራስ መተማመንን በማበልፀግ/በማዳበር ፅኑ ትጋት አድርጋለች። በምታስተምርበት ክፍል ውስጥ አንድ የተማሪዎች ቡድን ሠሌዳ ላይ፣ ሌላ የተማሪዎች ቡድን የሂሳብ ጥያቄዎችን በመፍጠር፣ እና ሦስተኛ ቡድን Chromebooks ላይ ትምህርት እየተከታተሉ ከፋፍላ ሁሉም በንቃት እንዲማሩ ታደርጋለች። ተማሪዎቹ ስለ እርሷ እንደሚሉት፣ ሁል ጊዜም ትምህርቱን እንድናውቅ ለመርዳት የምትችልበት መንገድ አታጣም፣ በፍጽም ተስፋ አትቆርጥም። በእርሷ እምነት "ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸው ፕሮብሌም የማቃለል ስሌት ዘዴ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ትምህርቱን ባለፈው ከተማሩት ጋር ማገናዘብ መቻልና ሂሳብን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናኘት አለባቸው።" ባልደረቦቿ እርሷን እጅጉን አወንታዊ ተሰሚነት ያላት እና የለውጥ ሃዋርያ ብለው ይጠሯታል። የተዋጣለት የግራንት ጥያቄዎችን ከመጻፏም በላይ በሰመር ወቅት በሼዲ ግሮቭ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በአውታረ መረብ በማስተማር የሂሳብ ትምህርት/online summer school math class at Shady Grove Middle School ፈር ቀዳጅ ናት። የአልጄብራ ተማሪዎችን ለማጠቃለያ ፈተና እንዲዘጋጁ ለመርዳት ከትምህርት ሠዓት በኋላ ፕሮግራም ታካሄዳለች፣ ተማሪዎችን ስለመጪው ፈተና ዝግጅት ለማድረግ እንዲችሉ ያላችውን እድሎች ለማስገንዘብ Algebra Town Hall ስብሰባዎችን በማደራጀት ታቀነብራለች።

—የሼዲ ግሮቭ/Shady Grove የሠራተኞች ሙያ ማበልጸጊያ መምህርት Christine Oxenford እንዳለችው፤ ችሎታዋ እና የምትከፍለው መስዋእትነት ከሚጠበቀው በላይ እንደሆነ ገልፃለች። "Her skills and dedication extend beyond what is expected," "ጭቅጭቆች ሲፈጠሩ መፍትሔ ስትፈጥርና ሌሎችም ከባድ ሁኔታዎችን በሚያስገርም ትዕግስት እና በሚያስደንቅ ዘዴ ስትፈታ አይቻለሁ። ሞቅ ያለና ደስታ የተሞላበት ዝንባሌ/አመለካከት ታሳያለች። ሰዎችን ትወዳለች፣ በጣም ጠንክራ በመስራት ሁልጊዜም በእርሷ ዙሪያ ያሉ ሰዎችን መንፈስ ታነቃቃለች።"

Janet Gallagher ከ 2015 ጀምሮ በሂሳብ ዲፓርትመንት የመገልገያዎች/resource መምህርት በመሆን አገልግላለች። ልዩ የሆነች መሪ - በደንብ የተሰናዳች/የተደራጀች፣ ግትር ያልሆነች እና የፈጠራ ክህሎት ያላት። የ Bethesda-Chevy Chase ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰመምህርት Donna Redmond Jones የሰየመቻት፤ ልዩ የማስተማር ችሎታ ወሳኝነት ባለው የሂሳብ ትምህርት ላይ ያልተዘመረላት፣ ስሟ ያልተጠራ ጀግና ናት "an unsung hero in the math classes where exceptional teaching matters most." በ 2016–2017 የከፍተኛ ደረጃ ምደባ ስታትስቲክስ ኮርስ እስከ 30 ፐርሰንት አፍሪካን አሜሪካን ወይም ላቲኖ ናቸው። እንዲሁም በMETS program ፕሮግራም ላሉ፣ከትምህርታቸዉ ወደ ኋላ ለቀሩና/ለተስተጓጎለባቸዉ እንግሊዘኛ ለሚማሩ ተማሪዎች ሂሳብ አስተምራለች። ለጉዳት የተጋለጡ/ደካማ ተማሪዎች ጋር ያገኘችው ስኬታማነት እርሷ ለምትመራቸው 19 ሠራተኞች እንደ ሞዴል/ተምሳሌትነት ያገለግላል። እኩልነት-እና ፍትሃዊነት እንዲሰፍን መሪ የመሆን ጥልቅ ፍላጎት አላት። ተማሪዎች እንዲማሩ ለመርዳት ወቅታዊ ምርምሮችን ራሷ በቋሚነት እያጠናች አዳዲስ ስልቶችን ስራ ላይ ታውላለች። ሥርአተ ትምህርት/ከሪኩለም ጽፋለች እናም የሙያ እድገት እድሎችን በየጊዜው ትከታተላለች። የመጀመሪያ ዓመት ጀማሪዎችን ለማደፋፈርና ከፍ ባለ ደረጃ የሂሳብ እና የሳይንስ ኮርሶችን እንዲወስዱ ለማበረታታት የSTEM ትብብሮሽ ታመቻቻለች። በአካባቢ ያለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በመጎብኘት በርካታ የስምንተኛ ክፍል ልጃገረዶችን የሂሳብን እና የሳይንስ ሥራዎችን በእጃቸው እየሠሩት እንዲገቡበት አድርጋለች። የማህበረሰብ አባላትን በ STEM መስኮች በጋራ በማሰባሰብ ፕሮብሌም በመፍታት እና በህብረት/በቡድን ገብተውበት እንዲሰሩ ሃሳብ ለማመንጨት የሚያስችል የርእሰመምህር STEM አማካሪ ቦርድ በማደራጀት ረድታለች።

የቤተዝዳ ቼቪ-ቼዝ ርእሰመምህርት ዶና ረድሞንድ ጆንስ (Bethesda-Chevy Chase Principal Donna Redmond Jones) እንደሚገልጿት፦- ወ/ሮ Gallagher የምትመራው፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች ከፍተኛ ግምት በመስጠት፣ በአንፃሩም ሁሉም እንክብካቤ እንደሚደረግለቸው የሚያስቡበት እና የሚደሰቱበት አካባቢ በማመቻቸት ምሳሌ በመሆን ነው።" እርሷን ይበልጥ ለሚፈለጉ ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ከፍ ባለ ደረጃ በማተኮር ምን ያህል በቁርጠኝነት እንደምትሠራ ተማሪዎችም ሆኑ ሠራተኞች ምንም ጥርጣሬ አይኖራቸውም። አቀራርቧ ረጋ ያለ ቢሆንም፣ ነገር ግን የእሷ ተጽእኖ በጣም ጥልቅ ነው።"

የ Greenblatt Education Fund በተጨማሪም የ2018 ገናና ኮከብ መምህራን ሽልማት የሚሰጠው ለ Erin Crowleyበ ሶመርሴት ኤለመንተሪ ት/ቤት (Somerset Elementary School) የሙዓለ ህፃናት አስተማሪ እና Helene McLaughlin በኖርዝዉድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Northwood High School) የፊዚክስ እና የጀነራል ሳይንስ መምህር ለሆኑት ነዉ። ይህ ሽልማት ፈጠራዊነታቸውና ጉጉታቸው ተማሪዎች እንዲነቃቁ/ራሳቸዉን እንዲያነሳሱ ተጨማሪ ግኝት እንዲያመጡ የሚያበረታታ ከአምስት አመት በታች ተሞክሮ ያላቸውን መምህራን ያከብራል።

ለአመታዊ መምህር ሽልማት የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪዎች፣ በMontgomery County አምስት እመት ወይም ከዚያ በላይ የማስተማር ተሞክሮ እንዲኖራቸው የሚገባ፣ በመምህራን ቡድን፣ በትምህርት ቦርድ አባሎች፣ በMCPS ሰራተኛ አባሎችና የMontgomery County Council of PTAs ተወካዮች፣ እንዲሁም ለ Greenblatt የቤተሰብ አባላት ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸዋል።

መምህራን፣ ከሌሎችም የMCPS ሠራተኞች እና አጋሮች ጋር ስላበረከቱት አስደናቂ ሥራቸው የልጆች ሽልማት ክብረ በአል/Children Awards Celebration አካል ዓመታዊ ሻምፒዮና በመሆን ይሸለማሉ። በGermantown, ብላክሮክ የስነጥበብ ማዕከል (BlackRock Center for the Arts) ረቡዕ፣ ኤፕሪል 18 በሚካሄድ ዝግጅት ላይ የ MCPS የዓመቱ መምህር ይሰየማል።

የ [Marian Greenblatt Fund](Marian Greenblatt Fund)፣ በቀድሞ የትምህርት ቦርድ አባል ስም የተሰየመ፣ ተማሪዎቻቸውን የግኝት ስሜት እንዲሰርፅባቸው ለሚያደርጉ መምህራን እውቅና ይሰጣል፣ ለልቀት እንዲጥሩ እና ት/ቤታቸውንና ማህበረሰባቸውን እንዲያግዙ ወጣት መምህራንን ያበረታታል። ድርጅቱ ለእያንዳንዱ የዓመቱ መምህር የመጨረሻ ዙር ተወዳዳሪ የ$2,000 ሽልማት፣ እና ለሁለቱ Rising Star Teaching ተሸላሚዎች ለእያንዳንዳቸው $1,000 ይሸልማል።

**የሙአለህፃናት መተዋወቂያ ኤፕረል 3 እንዲጀመር ተመደበ**

የ2018 የሙአለህፃናት መተዋወቂያ ሰሞን ኤፕረል 3 ይጀመራል። በመተዋወቂያው ወቅት፣ ወላጆችና ተማሪዎች ከት/ቤቱ ርእሰመምህር፣ የሙአለህፃናት መምህራንና ከሌሎች የስራ ባልደረቦች ጋር ይገናኛሉ።

ክፍለጊዜያቱ— በእያንዳንዱ የኤለመንተሪ ት/ቤት በኤፕሪል 3 እና ሜይ 26—መካከል የተያዙት ሴፕቴምበር 1/2018 አምስት ዓመት እድሜ ለሚሆናቸው ልጆችና ለወላጆቻቸው ነው። ወላጆች ወደ አካባቢያቸው ት/ቤት በመደወል ለዚያ ት/ቤት በተወሰነ ቀን ለመመዝገብ ቀጠሮ መያዝ አለባቸው። የትኛው ኤሌሜንታሪ ት/ቤት አካባቢያቸውን እንደሚያገለግል እርግጠኛ ያልሆኑ ወላጆች በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4700 Boundaries Office መደወል ወይም የMCPSን ድረገጽ School Assignment Locator (የት/ቤት ምደባ ጠቋሚ) ማየት አለባቸው።

የሙአለህፃናት መረጃዎች

**አዲሱ ድረገጽ የሚያመለክተው የ MCPS ን ተመራቂዎች በተሳካ ሥራ ላይ ነው**

የ MCPS የሥራና ቴክኖሎጂ ትምህርት ፕሮግራሞችን/Career and Technology Education (CTE) programs እና የሚሰጡትን ጥቅም ለማስተዋወቅ ዲስትሪክቱ ከሚያደርጋቸው ጥረቶች እንደ አንዱ አካል MCPS የጊዜ ቅደምተከተልን የጠበቀ በተዋጣላቸው ሥራ ላይ ያሉ የMCPS ተመራቂዎችን ታሪክ ማቅረብ ጀምሯል። MCPS አጭር የህይወት ታሪክ/ገጽታ የሚያሳዩ የጽሑፍ እና የቪድዮ ትረካዎችን እያደራጀ ሲሆን እስከ ዓመቱ መጨረሻም ማሰባሰቡን ይቀጥላል። እነዚህ ታሪኮች ስለ ስኬታማነት አጫጭር ገጽታዎች ድረገጽ ላይ ይገኛሉ

MCPS በፋይናንስ፣ በህግ፣ በትምህርት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እና በኮንስትራክሽን ዘርፎች እየሰሩ ያሉ ተመራቂዎች አሉት። ከ MCPS ያገኙትን ትምህርት እና ልምድ ትልቅ ዋጋ በመስጠት ከዳርቻ የሚያደርሱት በኮሌጅ፣ በድህረ ምረቃ ት/ቤት፣ በኢንተርንሽፕ እና በሥራዎቻቸው ላይ ተግባራዊ በማድረግ ነው።

**የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተመጻሕፍት/ላይብራሪዎች ስለ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብ/ Science, Technology, Engineering, and Mathematics (STEM) ስማርት ፕሮግራሞችን በነፃ ያቀርባሉ።**

የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተመጻሕፍት/ላይብራሪዎች ስለ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብ/ Science, Technology, Engineering, and Mathematics (STEM) ስማርት ፕሮግራሞችን ከ 10 እስከ 14 ዕድሜ ላላቸው ልጆች በነፃ ያቀርባሉ። ተማሪዎች ስለ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ኢንጂነሪንግ፣ እና ሒሳብ/ Science, Technology, Engineering, and Mathematics (STEM) በእጃቸው እየሠሩ ሙከራዎችን እያደረጉ የመማር እድል ይኖራቸዋል። እነዚህ ፕሮግራሞች የሚመሩት ጡረታ ወጥተው ከ American Association for the Advancement of Science (AAAS) STEM volunteer program and Adventures in Science በበጎ ፈቃደኝነት በሚያገለግሉ ሳይንቲስቶች ነው።

ልጆች በሁሉም ክፍለጊዜ ለመሳተፍ ይችላሉ ወይም የሚፈልጉትን ክፍለጊዜ ለመምረጥ ይችላሉ። ለእያንዳንዱ ክፍለጊዜ ምዝገባ ያስፈልጋል። ሁሉም ፕሮግራሞች የሚጀምሩት በ 2 p.m ነው። እዚህ ይመዝገቡ

Davis, 6400 Democracy Blvd., Bethesda

- ማርች 17: ኪችን ኬሚስትሪ/Kitchen Chemistry
- ማርች 31: ፈሳሽ ነገሮች ጠጣር ነገሮችን ወደላይ በሚያንሳፍፉበት ጊዜ/Buoyancy/Archimedes — When Liquids Push Objects Up!

- ኤፕሪል 14: የወንጀል ምርመራ ሳይንስ/Crime Science Investigations — Escape Room
- ኤፕሪል 28: ቸኮሌት/Chocolate
- ሜይ 12: ኤሌክትሮኒክስ/Electronics

Gaithersburg, 18330 Montgomery Village Ave.

- ማርች 18: ስትራውበሪ/Strawberry DNA
- ኤፕሪል 15: በኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ መደሰት/Fun with Computer Programming
- ኤፕሪል 29: ኤሌክትሮኒክስ/Electronics
- ሜይ 13: በኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ መደሰት/Fun with Computer Programming

Silver Spring, 900 Wayne Ave.

- ማርች 25: ኪችን ኬሚስትሪ/Kitchen Chemistry
- ኤፕሪል 8: ቦያንሲ አርኪመደስ/ፈሳሽ ነገሮችን ጠጣር ነገሮችን ወዳላይ በሚያንሳፍፉበት ጊዜ/Buoyancy/Archimedes — When Liquids Push Objects Up!
- ኤፕሪል 22: የወንጀል ምርመራ ሳይንስ/Crime Science Investigations — Escape Room
- ሜይ 6: ቸኮሌት/Chocolate
- ሜይ 20: ኤሌክትሮኒክስ/Electronics

**ፕሮግራሞቹ ስፖንሰር የሚደረጉት በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የአካባቢ ቤተመጻሕፍት/የላይብራሪ ቻፕተር ወዳጆች ነው።**

የ AAAS Stem volunteer በጎ ፈቃደኞችን እየመለመለ ነው። ፍላጎት ካለዎት Robert Thomas ን በስልክ ቁጥር፦ 301-570-2811 ያነጋግሩ። ስለ ፕሮግራሙ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማወቅ Mary Ellen Icaza ን በስልክ ቁጥር 240-777-0006 ያነጋግሩ።

**የMCPS ወጣቶች ለ MoCo's Got Talent Show (የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተሰጥኦ ያላቸው ትእይንት ለማሳየት) በእጩነት እንዲወዳደሩ ተጋብዘዋል**

**ተሰጥኦ ላላቸው ለሁሉም ወጣቶች ጥሪ! ልጅዎ መጨፈር፣ መዝፈን፣ ስነ-ስዕል ወይም ግጥም መፃፍና ማንበብ ይወዳል/ትወዳለች ወይ?**

በ MCPS መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ ለአምስተኛው ዓመት የ *MoCo's Got Talent* ትእይንት በሲልቨርስፕሪንግ በሚገኘው ፊልሞር (Fillmore in Silver Spring) **እሑድ ሜይ 20 በሚካሄደዉ ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል።**

**ተሳታፊዎች ለመመዘኛው በቅድሚያ መመዝገብ አለባቸው** [በ ActiveMONTGOMERY.org]፣ **ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የአንዱን ቁጥር በመጠቀም። በጠቅላላ በካውንቲው ውስጥ በአምስት ቦታዎች ከዚህ በታች በተጠቀሱት ቀናት ምዘናዎች ይካሄዳሉ። ከምዝገባ በኋላ ተሳታፊዎች የ** audition **ጊዜ እና** slot **ለመያዝ እንዲሁም እንዴት የስነጥበብ ሥራ ለማቅረብ እንደሚቻል በዝርዝር ለማወቅ/ለመረዳት በስልክ ቁጥር፡- 240-777-8080 መደወል ይኖርባቸዋል።**

| **ቀን** | **ቦታ** | **ሰዓት** | **እንቅስቃሴ/ተግባር** |
|---|---|---|---|
| **ማርች** 16 | ኢስት ካውንቲ የማህበረሰብ መዝናኛ ማዕከል | 5-9 p.m | 49619 |
| **ማርች** 24 | Holiday Park Senior Center | 1-4 p.m | 49625 |
| **ኤፕረል** 6 | North Potomac Community Recreation Center | 5-9 p.m. | 49621 |
| **ኤፕረል** 13 | Wisconsin Place Community Recreation Center | 5-9 p.m. | 49622 |
| **ኤፕረል** 20 | Upper County Community Recreation Center | 5-9 p.m | 49620 |
| **ኤፕረል** 20 | **የስነጥበብ ሥራዎችን ለማቅረብ**/Visual Arts Submissions | | 49678 |

**ሦስት የችሎታ/ተሰጥኦ ዘርፎች አሉ፤ ሙዚቃ** (Music)፣ **ዳንስ** (Dance)፣ **እና ስነ-ስዕል** (Visual Arts) **ተሳታፊዎች ከአንድ ዘርፍ በላይ ሊገቡ/ሊሳተፉ ይችላሉ። ቡድኖች እና የሙዚቃ ባንዶች ሊመዘገቡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሁሉም አባላት የብቃት መመዘኛዎችን ማሟላት ይኖርባቸዋል። የስነ-ስዕል ስራዎች የሚቀርቡበት ቀን ኤፕሪል**/April 20 **ነው።**

**ከእያንዳንዱ** audition **ምርጥ/ከፍተኛ ተዋናዮች ለማጣሪያ ውድድር የሚጋበዙበት ቀን** April 28 **ነው። ማጣሪያውን ያለፉት 12 ምርጥ ተዋናዮች** MoCo's Got Talent **በ** Fillmore Silver Spring **ሜይ**/May 20 **በምርጥ ተዋናይነት ያቀርባሉ።**

በእያንዳንዱ ዘርፍ ለአሸናፊዎች የተዘጋጀ ሽልማት ጁላይ 5 በሲልቨርስፕሪንግ/Silver Spring የሚካሄደውን የሰመር ኮንሰርት/Silver Spring Summer Concert እና ኖቬምበር 17/2018 የሚካሄደውን የሞንጎመሪ ካውንቲ Thanksgiving Parade ላይ መሳተፍን ያካትታል።

MoCo's Got Talent የሚያገለግለው በፈጠራ ችሎታ መግለጫዎችን፣ እና ወጣቶችን ከፍተኛ ፍቅር/ስሜት እንዲያካፍሉ እና ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱ ለማነቃቃት ነው። የውድድሩ ዓላማ በሞንጎመሪ ካውንቲ ውስጥ የስነጥበብ ፍላጎትን ለማስፋፋትና በወጣቶች ህይወት ውስጥ የስነጥበብ አስፈላጊነትን ለማስተጋባት ነው።

ለምዝገባ፡- www.activemontgomery.org ይጎብኙ። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 240-777-8080 ይደውሉ።